# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 1 ቁጥር 43 ግንቦት 22 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ


# አባይ እና እኛ !



## ነፃ ሀሳብ

# አባይ እና እኛ!

## እንደ መግቢያ

በዓለማችን በሕዝብ ብዛቷ በመጀመሪያው ረድፍ ላይ የምትገኘውና ሁለተኛውን የዓለም ኢኮኖሚ እየመሰረተችያለችው እስያዊቷቻይና፣ትልቁ የኃይል ማመንጫ ግድቧ ለእድገቷመሰረቷእንደሆነ ይታመናል:: ለሕንድም ሆነ ለአሜሪካ እድገት ከውሃ የሚመነጭ ኃይልወሳኝ ሚና ተጫውቷል፤ እየተጫወተም ይገኛል::አፍሪካ በዚህ ዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ልትገኝ የቻለችው የውሃ ኃይሏን መጠቀም የሚያስችል የአቅም ውስንነት ስላለበት መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል:: ሀገራችን ኢትዮጵያምሕዝቧን ከድህነት ለማላቀቅየውሃ ኃብቷን ለመጠቀም የሚያስችል አቅምአልነበራትም::ወንዞቿዋ ለእድገቷ የሚኖራቸውን እምቅ ኃይል ለመረዳት የሚያስችል ፖለቲካዊም ሆነ ኪነ-ጥበባዊ ቁጭት መኖሩን ግን አሻራችን ይመሰክራል:: ስለወንዞቻችን ተዚሟል፤ ተጽፏል::በተለይም የአባይ ወንዝ የዘመናት ቁጭታችን ሆኖ ኑሯል:: በቁጭት ስናንጎራጉር የኖርነው የዘመናት ህልም ነበር:: በተለያዩ ጊዜያት ቢታሰብም ያልተሳካውን ህልምእውን ለማድረግ የመሰረት ድንጋይ ከዘጠኝዓመታት በፊት በ2003 ዓ.ም በወርሃ መጋቢት በሕወሓት/ኢህአዴግ ዘመን መጣሉ ይታወሳል::

ቀጣይነት ያለው የሀገር እድገት ያላስመዘገብነው፤ የተቀላጠፈ ማኅበራዊ አገልግሎት የሌለን እና የሥራ እድሎችን በበቂ ሁኔታ ያልፈጠርነው፤ ለፖለቲካ ፍጆታ ሳይሆን እውነተኛና የሕዝብ የኑሮ ለውጥ ላይ የሚነበብ የኢኮኖሚ እድገት ያላስመዘገብነውኢንደስትሪው ባለ መስፋፋቱ መሆኑን ብዙዎችን ያስማማል:: የዚህ ሁሉ መሰረታዊ ችግር ደግሞ የኃይል እጥረት መሆኑ ይታወቃል::በዋነኝነት አሁን ሀገራችን ያላት አቅም ላይ ከእጥፍ በላይ የኃይል አቅርቦቱን ለመጨመር ታስቦ ግንባታው መጀመሩን ሀገራችን ስትገልፅ እንደነበር የሚታወስ ነው:: ያ ህልም ነው ያኔ መሰረቱ የተጣለው:: ያንን



ህልም እውን ለማድረግ ነው የሀገራችን ሕዝብ ከአፋኙ የሕወሓትአገዛዝጋር የተባበረው:: ታሪክ የሚሠራው በእንዲህ ዓይነት ሁኔታም ጭምር ነው ::

## የአባይ ግድብ እና ሕወሓት

አንዳንድ ወገኖች በግድቡ ዙርያ የተለያዩ የቅሬታ ሃሳቦችን እያቀረቡ እንደነበርይታወሳል:: ከግድቡ መጠን እስከሚሰጠው አገልግሎት፤ ከቦታው ለሱዳን ቅርብ መሆን እስከ የገንዘቡ መጠን ወዘተ... የተለያዩ ኃሳቦች በድጋፍም በተቃውሞም ተሰንዝረዋል:: ገሚሱ ሕወሓት/ኢህአዴግ በወቅቱ በቂ መረጃ ባለመስጠቱ፤ ገሚሱ ግድቡን ሕወሓት/ኢህአዴግ ለፖለቲካ ፍጆታ ለማዋል በመሞከሩ ይህም የብዙ ወገኖች ስምምነት የሌለውን የግንቦት 20 በዓልን ከአቶ መለስ ዜናዊ እረፍት በኋላ በታላቁ የኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ ላይ እስከማክበር በመሄዱ እንዲሁም ከፉኛ ተንሰራፍቶ በነበረው የሙስናው ሁኔታ ባስከተለው ቅሬታ የተመዘገቡ ተቃውሞዎች እንደነበሩ ይታወሳል::ይህም ሆኖ በጥቅሉ ሲታይ ሕወሓትን እና አቶ መለስ ዜናዊን በሀገራችን ታሪክ በበጎ ጎኑ የሚያነሳቸው ከሆነ አንዱ እና ትልቁ ተግባራቸው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ነው የሚሉ ድምፆች ይሰማሉ:: የዚህ ፅሁፍ አቅራቢም በዚህ ይስማማል:: የአቶ መለስ ዜናዊ እና የድርጅታቸው ጨቋኝ ጫማ ተቀናቃኞችን ምን ያህል ረግጦ እንደኖረ ከሀገር አልፎ ዓለም ያወቀውእውነታ በመሆኑ እዚህ ጋር አላነሳውም::ታላቁ የሕዳሴ ግድብ መሰረቱ ከተጣለበት ቀን አንስቶአሁን ያለበት ደረጃ እስኪደርስ ድረስሕዝብ በጉጉት ▶

▶ ሲጠብቀው የቆየ ሀገራዊ ፕሮጀክት ሆኗል :: ይህ በእንዲህ እንዳለ ሕወሓት በዚህ ወቅት እንደ ድርጅት ከዚህ በተፃራሪ ቆሟል :: ሀገራችን ሰላም ኑሯት፤ ሕዘቡ በአንድነት የተጀመረውን ግዙፍ ሀገራዊ ፕሮጀክት እንዳያሳካ የተለያዩ አሜኬላዎችን በመትከል እንደ ሀገር ሰላም እና አንድነት እንዳይኖረን እየሠራ ነው:: ጭቆና እና አድልዎን መታገል የሁላችን መሆን ይገባዋል::እንደ ሕዝብ በተለየ የተጨቆነ ሕዝብ ሆነ ኃይል መኖሩን ባልተከሰተበት ሁኔታ የራሱን ድርጅታዊ ጥቅም ከሀገር ጥቅም በማስቀደም ፕሮጀክቱን ለማደናቀፍ መሞከር ከታሪክ ተወቃሽነት አያድንም:: በግድቡ ዙሪያ የአቶ መለሰን

> ‹‹ሀገራችን ሰላም ኑሯት፤ ሕዘቡ በአንድነት የተጀመረውን ግዙፍ ሀገራዊ ፕሮጀክት እንዳያሳካ የተለያዩ አሜኬላዎችን በመትከል እንደ ሀገር ሰላም እና አንድነት እንዳይኖረን እየሠራ ነው::››

ሌጋሲ ለማስቀጠል በርካታ የሕወሓት አባላት እና ከፍተኛ አመራሮች የሆኑም የነበሩም ገንዘባቸውን፣ እውቀታቸውንናጊዜያቸውን በመሰዋት ሌት ተቀን በቅንነት እና በታማኝነት እየሠሩ መሆኑን የምንገነዘበው እውነታ ነው :: ከአቶ መለስ ዜናዊ በተቃራኒ የቆመው ያኔም የነበረአሁንም የወቅቱ የሕወሓት ከፍተኛ አመራር ሆኖ ይታያል:: ይህም የአቶ መለስ ዜናዊን ሃሳብ መረዳት ባይቻልም የሕወሓት አመራር ግን ፕሮጀክቱን ለቡድናዊ የጋራ የሃብት ምንጭነት ወስዶት እንደነበር ይገመታል:: ከአሁኑ አቋም ጋር ሲነፃፀር ማለት የሚቻለው ይህንን ነው ::

## አባይ እና “እኛ-ተቀናቃኞች”

ሁኔታዎች በተስተካከሉበት ሀገር የፖለቲካ ተቀናቃኝነት ከገዥዉ ፓርቲ የተሻለ የሃሳብ ባለቤት መሆን ነው:: ገዥው ፓርቲ እንደ መንግሥት ሊፈፅመው ያልቻለን አማራጭ ሀሳብ በመያዝ ሕዝብን በማሳመን ሀሳብን ሸጦ ስልጣንን መረከብ ነው:: የሀገራችን ሁኔታ ከዚህ እሳቤ እንደሚለይ ይታወቃል:: ኪሳችን ብቻ ሳይሆን ሃሳባችንም ድሃ ነው::ያሳለፍነው የጭቆና ዘመናት እንዲህ እንዳናስብ አድርጎናል:: ትግላችን ሁሉ ከነፃነት ጋር የተያያዘ ስለነበር የሃሳብ ፈተና አልነበርም::በዚህ ሁኔታ እዚህ ዘመን ላይ ደርሰናል:: የሀገራችን ፖለቲካ በብዙ መልኩ ተበላሽቷል::አስተካክሎ መጓዝ ከፊታችን ያለው ብቸኛ ምርጫ ነው:: ባለንበት ሁኔታ ተጨማሪ ድንጋይ መወራውርን የሚፈቅድ አይመስልም::ፖለቲካችን ብቻ ሳይሆን የሕዝባችን ህልውና ፈታኝ ሁኔታ ላይ ይገኛል::መቻቻል እና መወያየት ግዴታችን ሆኗል::ከዚህ መስመር ስንዝር ፈቀቅ ካልን ጉዳቱ ለሁላችን ይሆናል:: በዚህ መሃል የአባይ ጉዳይ ልዩነት መፍጠር አይኖርበትም:: በሀገረ ኢትዮጵያ የሚያምን ወገን ሁሉ በአባይ ጉዳይ ላይ ልዩነት ሊኖረው አይገባም::እንቅፋት ለመሆን መሞከር በጨለማ ከሚኖር ሕዝብ ወጥቶ በብርሃን ለሚኖሩ ግብፃውያን ስልታዊ ድጋፍ እንደመስጠት ያስቆጥራል:: ሕዝብ ይህንን የመሰለ እንቅፋት ዝም ብሎ የሚያይበት ጊዜ ያለፈ ይመስላል:: በመሆኑም የፖለቲካ ተቀናቃኝ ከሆኑ ወገኖች ስለ አባይ ጉዳይ ከገዥው ፓርቲ እና መንግሥት የተሻለ ገንቢ ሃሳብ ማፍለቅ ባይችሉ እንኳን አሰላለፋቸውን ከሕዝብ እና ከመንግሥት ጎን መሆን ይገባዋል፤ ይገባናል:: መንግሥትምይህን ጉዳይ፣ ይህን ችግር በሰከነ ሁኔታ ለተቀናቃኝ ወገኖች ሕዝብ የሚሰማው የውይይት መድረክ ማዘጋጀት ግዴታ እና ኃላፊነቱ አለበት::የገዥዎች ወንዝ የማያሻግር ብልጠት እዚህ አድርሶናልና:: የኢዜማ እምነት ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ጉዳይ ከኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ በተጨማሪ ፖለቲካዊና በአካባቢዉ ሀገራት ፍትሃዊ የሃብት አጠቃቀምን ጥያቄ ያዘለ ጉዳይ ሆኗል የሚልነው::በሀገር ውስጥም አንድ ሕዝብን በብሄራዊ ኩራትነት የማሰባሰቢያ አጀንዳ ሆኖ ይገኛል::ለዚህ ግድብ መሠራትሕዝብና ሃገር ውድ ዋጋ ከፍለውበታል፤ እየከፈሉበትም ይገኛል:: ለቀጣዩ ትውልድ የሚተላለፍ የዚህ ትውልድ አሻራም ነው::የአካባቢው ጂኦፖለቲካዊ አብይ ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን ኢዜማ ግድቡን ▶


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ግንቦት 22 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ



ለማጠናቀቅ ከመንግሥት ጎን ልንቆም ይገባል የሚል አቋም አለው፡፡ ግድቡ አሁን ያለበትን ሁኔታ መንግሥት ለሕዝቡ ክፍትበማድረግ ግልፅ ሊያደርገው ይገባል፡፡ግድቡ በተያዘለት ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቅ ኢዜማ የበኩሉን ድርሻ እንደሚወጣ ከዚህ በፊት መግለፁ ይታወሳል፡፡ከቀዳሚ አጀንዳዎቹ አንዱ ተደርጎም ተይዟል፡፡ሀገራችን የሕዳሴውን ግድብ ጨምሮ ከሠራቻቸው እና እየሠራቻቸው ካሉት ታላላቅ ፕሮጀክቶች ልምድ በመነሳት ያላትን ሁለንተናዊ ሃብት ተጠቅማ ተጨማሪ ለዘላቂ እድገትና የኢኮኖሚ መዋቅር ሽግግር የሚጠቅሙ ሜጋ ፕሮጀክቶችን እንድትሠራ ኢዜማ ቁርጠኛ አቋሙ መሆኑ ግልፅ አድርጓል፡፡ኢዜማ የሀገር ብሔራዊ ጥቅምና ሉአላዊነት ለድርድር የማይቀርቡ፤ በሁሉም ለሀገር ጥቅም የቆሙ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ ስምምነት ሊኖራቸው የሚገቡከፖለቲካ ጥቅም በላይ የሆኑ አጀንዳዎች ናቸው ብሎ ያምናል፡፡ለዚህም ከማንኛውም ሀገራዊ ኃይል ጋር በትብብርና በአንድነት ይሠራል፡፡ የጸሐፊውም እምነት ተመሳሳይ ነው፡፡ የሀገር እና ሕዝብ ልዓላዊነት ለድርድር መቅረብ የለበትም፡፡ሕዝብምከእኛ ከተቀናቃኞች የሚጠብቀው ይህንን ነው፡፡

## ስጋቶች

ግብፅ የግድቡን ግንባታ ለማስተጓጎል እንቅልፍ አጥታ እየሠራች ነው፡፡ ዜጎቿ እና ሁሉም ተቋማቶችዋ ልዩነት ሳይኖራቸው በግድቡ ጉዳይ እየሠሩ ይገኛሉ፡፡በርካታ ተፅዕኖዎችን በሀገራችን ላይ ያስከተሉ ቢሆንም ሊያስቆሙን አልተቻላቸውም፡፡ እኛ የነሱን ያህል በተለይም በዲፕሎማሲው እና ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የተጠናከረ መረጃ በማድረስ በኩል ያን ያህል እየሠራን እንዳልሆነ ብዘዎች ይስማማሉ፡፡ ግድቡን ሠርተን በማጠናቀቅ እና ለረዥም ዓመታት ሥራ ላይ ለማዋል በርካታ

‹‹ከአቶ መለስ ዜናዊ በተቃራኒ የቆመው ያኔም የነበረአሁንም የወቅቱ የሕወሓት ከፍተኛ አመራር ሆኖ ይታያል፡፡ ይህም የአቶ መለስ ዜናዊን ሃሳብ መረዳት ባይቻልም የሕወሓት አመራር ግን ፕሮጀክቱን ለቡድናዊ የጋራ የሃብት ምንጭነት ወስዶት እንደነበር ይገመታል፡፡››

ስጋቶች እንደሚገጥሙን ይታመናል፡፡ግድቡ ተጠናቆ የውሃ ሙሊቱ ከፍ እስከሚል ድረስ ግብፅ ስጋታችን ሆና ትቀጥላለች፡፡ በርካታ ባለሙያዎች እንደሚጠቁሙት የአካባቢ ጥበቃ በተለይም በአባይ ተፋሰስ ላይ በቂ የአፈርና የውሃጥበቃ አለመሠራቱ ሌላኛው ስጋት ነው፡፡ ደለል ያበላሸብን ትናንሽ ግድቦች ለዚህ አስረጂ ይሆናሉ፡፡እንደ መስኩ ባለሙያዎችስጋት እንቦጭ የታላቁን የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ምንጭ የሆነውን የጣና ሃይቅንአልፎ ራሱን ግድቡን የሚያጠቃ ትልቅ አደጋ ይሆናል፡፡ በዚህ በኩልምችግሩን ለመቅረፍ በቂ የሆነ እንቅስቃሴ ባለማድረግ የፌደራል መንግሥቱ ተወቃሽ እና ተጠያቂ ነው፡፡ በቀጣይ መንግሥትሊሆኑ የሚችሉ ፓርቲዎች ፈተናሆኖ ይዘልቃል፡፡ ፖለቲካዊ ስክነት እና ሀገራዊ መግባባት ካልመጣም ቀጣዩ ስጋታችን መሆኑ አይቀሬነው፡፡እነዚህን እና ሌሎች ስጋቶችን በመቅረፍ ለሁላችንም የምትመች ሀገር ለትውልድ ለማስረከብ መነጋገር መነጋገር አሁንም መነጋገር ወሳኝ ነጥብ መሆኑ የብዙዎች እምነት ነው፡፡ለማጠቃለልአባይ ይገደባል፤ ጨቋኝ መንግሥት መሆን የሚመኝም ከሥልጣኑ ይወርዳል!!!ሕወሓት/ኢህአዴግ ጋር የሆነውም ይኸው ነው!!!

የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ የሆኑት አቶ ተክሌ በቀለ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ናቸው፡፡ በሚከተለው የኢሜይል አድራሻቸው በኩል ፀሐፊውን ማግኘት ይቻላል፡- tekleb2006@gmail.com



# <<ይህን ወረርሽኝ እንደ ፖለቲካ መሳሪያ መጠቀም በማኅበረሰቡ ዘንድ ትዝብት ውስጥ የሚጥል ያነሰ ተግባር ነው>> ዶ/ር ሙሉዓለም ተገኘወርቅ

ዶ/ር ሙሉዓለም ተገኘወርቅ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የጤና ፖሊሲ ቡድን አስተባባሪ እና የኮቪድ 19 ግብረ ኃይል ሰብሳቢ ናቸው፡፡ ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ ያሉን ጥያቄዎች እንዲመልሱልን እንግዳችን አድርገን ጋብዘናቸዋል፡፡ ዶ/ር ሙሉዓለም ለቃለ ምልልሱ ፍቃደኛ ስለሆኑ በአንባቢዎቻችን ስም እናመሰግናለን፡፡ መልካም ንባብ!



**የኢዜማ የጤና ፖሊሲ ቡድን የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን ከመከላከል አንፃር ምን እየሰራ ይገኛል? ምን ሲሰራስ ነበር? ምን ለመስራትስ አቅዷል?**

የፖሊሲው ቡድን ስራው በምን አይነት ፖሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ መሰል ወረርሽኝ ቢመጣ ልንቋቋመው እንችላለን የሚለውን መንደፍ ነው፤የቡድኑ ስራ እንደ ኮሮና አይነት ማኅበረሰብ አቀፍ ወረርሽኞች በፖሊሲ ደረጃ እንዴት ይታያሉ የሚለው በፖሊሲያችን ውስጥ ማካተት ነው ያንን አድርጓል፡፡እኔ እንደ የፖሊሲ ቡድኑ አስተባባሪነቴ የኮቪድ-19 የኢዜማ ግብረ ሃይልን በሰብሳቢነት እየመራሁ የምገኝ ሲሆን ማኅበረሰቡን ግንዛቤ የማስጨበጥ እና ማኅበራዊ ግዴታን የመወጣት ስራ ለመስራት ከተቋቋመው የኮሚቴው አባላት ጋር በመሆን ወረዳዎችን በማስተባበር እየሰራን እንገኛለን፡፡ ከኮሚቴው መመስረት በኃላ በተለያዩ አካባቢዎች የተፈጠረውን የደም እጥረት ለመቅረፍ ባሰናዳነው የደም መለገስ መርሃ ግብር ላይ የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮችን ጨምሮ በሃገር አቀፍ ደረጃ ያሉ አባሎቻችን ዘመቻውን ተቀላቅለው ደም እንዲለግሱ አድረገናል፡፡የተወሰኑ የምርጫ ወረዳዎች ደግሞ እርዳታ ለሚሹ ወገኖች ድጋፍ አድርገዋል፡፡በቀጣይ ደግሞ ማኅበረሰባዊ ሃላፊነታችንን ለመወጣት እያንዳንዱ የምርጫ ወረዳ በየአካባቢው‹‹አሁንም እጠንቀቅ፤ አንዘናጋ!››በሚል መርህ ሕብረተሰቡን የማንቃትና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ከግንቦት 27 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ለመስራት ዝግጅቶች እየተደረጉ ይገኛል፡፡ከዚሁ ጋር ተያይዞም እያንዳንዱ ወረዳ በዚህ ዘመቻ ላይ በንቃትእንዲሳተፍ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡

**የኮሮና ቫይረስ ከሌሎች ከተሞች በተለየ አዲስ አበባ ላይ በከፍተኛ ቁጥር እየተስፋፋ ይገኛል፡፡ይህ ሊሆን የቻለው በምን ምክንያት የተነሳ ነው?**

የኮሮና ተጋላጭነት የሚጨምረው በንክኪ መሆኑን እስካሁን ባለው ጥናት የታወቀ ነው፡፡ አዲስ አበባ ደግሞ ከሌላው ዓለም ጋር የምንገናኝባት ዋና ከተማችን ናት፡፡ስለዚህም ዋነኛ የቫይረሱ መግቢያ በር ነች ማለት እንችላለን፡፡ ከዛም በላይ የማኅበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ፣ የዕለት ጉርሱን ለማግኘት ያለው መስተጋብር፣ የትራንስፖርቱ፣ የንግዱ፣ የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማቱ ብዛት፣ ያለው የኗሪ ብዛት ለቫይረሱ ስርጭት የየራሳቸውን ድርሻ የሚወስዱ ይሆናል፡፡በዚህ ሁኔታ ላይ መዘናጋት እና ቸልታ ስትጨምርበት ደግሞ የመስፋፋቱን እድል በእጥፍ የመጨመር ምክንያት እንደሚሆን መናገር ይቻላል፡፡

**በቅርብ ቀናት እንደታዘብነው አዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች በስፋት በቫይረሱ እየተያዙ ይገኛል፡፡ አብዛኞቹ ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ የጉዞ ታሪክ የሌላቸውም ሆነ በቫይረሱ ከተያዙ ሰዎች ጋር ንክኪ እንደሌላቸው ሲገለፅ እየሰማን እንገኛለን፡፡ አንድ ሰው በቫይረሱ ከተያዘ በኋላ መያዙን ሳያውቅ ለሌላ ሰው የማስተላለፍ እድል እንዳለው ይታወቃል፡፡ ታዲያ ይህ የቫይረሱ ባሕርይ እየታወቀ ሳለ የሚያዙ ሰዎችን በቫይረሱ ከተያዙ ሰዎች ጋር ንክኪ ያልነበራቸው ብሎ እንዴት መግለፅ ይቻላል?**

የአገላለፁ መንገድ ዓላማ የቫይረሱን ስርጭት ማኅበረሰባዊ መስፋፋት ለማሳየት ተብሎ ይመስላል፡፡ በእርግጥ ይህ አይነቱ አገላለጽ ትንሽ ግራ ያጋባል፡፡ሆኖም ግን በቫይረሱ የተያዙት ሰዎች ቀጥተኛ የሆነ

ግንኙነታቸውን ማወቅ በሚያስቸግርበት ጊዜ ነው ይህን አይነት ገለጻ ሲጠቀሙ የሚሰማው:: እንደው ለማሳየት ያህል ምንም ምልክት የማያሳይ‹‹ሀ››የተባለ ግለሰብ‹‹ለ››ከሚባል ግለሰብ ጋር ንክኪ ሲኖረው‹‹ለ››ያልነው ግለሰብ በተመሳሳይ ምንም ምልክት ሳይኖረው‹‹ሐ›› ለተባለው ሰው ያስተላልፋል ማለት ነው::ይህ‹‹ሐ››ያልነው ግለሰብ ሲመረመር ቫይረሱ ይገኝበታል ማለት ይሆናል:: በዚህ ምክንያት ይህ ግለሰብ ቫይረሱን ከየት እንዳገኘው በእርግጠኝነት ለመናገር ፍንጭ ሲጠፋ የጉዞ ታሪክም ሳይኖረው ሲቀር እየተጠቀሙት ያለው ገለጻ ይመስላል::ከገለፃው ባሻገር ልንገነዘበው የሚገባን ትልቁ መልዕክት ላይ ማተኮሩ የተሻለ ነው:: ያ መልዕክትም ቫይረሱ ያለባቸው ዜጎች ቁጥር ቀላል እንዳልሆነና ይህ ቫይረስ በማኅበረሰቡ ውስጥ እየተሰራጨ ነው ማለት ነው::

**በየቀኑ ከመመርመር በተጨማሪ ወረርሽኙን ለመቆጣጠር ምን አይነት አማራጮች መከተል አለብን ይላሉ?**

እስካሁን ባለን እውቀት እና መረጃ ላይ ተመስርተን ልንል የምንችለው ነገር ቢኖር በስፋት መመርመር እና ማኅበረሰቡ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ማስተባበር ነው:: እያንዳንዱ ዜጋ እንደ ግለሰብ የሚወስደው ጥንቃቄ ነው፤እንደ ሃገር ቫይረሱን መቆጣጠር እንድንችል የሚረዳን::ከዚህ በተረፈ ግን ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የመለየትና ልዩ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ስራ ነው ብዬ አምናለሁ::

**ቫይረሱ የማኅበረሰብ ስርጭት አድማሱ በከፍተኛ ቁጥር እየጨመረ እንደሆነ እየተመለከትን እንገኛለን:: ይህን የማኅበረሰብ ስርጭት ለመግታት ምን መደረግ አለበት ብለው ያስባሉ?**

የማኅበረሰቡ ስርጭትን ለመግታት መደረግ ያለበት ዋነኛው ነገር ማኅበረሰቡን ግንዛቤ ማስጨበጥ ላይ ባለመታከት በተለያዩ መንገዶች መስራት ነው::ካለንበት ሁኔታ አንጻር ያዝ ለቀቁ የትም አያደርሰንም:: ይህም ማለት ከአቅም በላይ መስራት ልንለው



‹‹እንደ ፓርቲ ከሁሉም በፊት መግለጫ በማውጣት የተለያዩ ምክረ ሃሳቦችን አቅርበን እንደነበር ይታወሳል:: ያነሳናቸው ምክረ ሃሳቦች ተግባራዊ ተደርገዋል ብለን እናምናለን:: እንደምሳሌ በተደጋጋሚ ስንል የነበረው በቋሚነት ለማኅበረሰቡ መረጃማ ድረስ ላይ ከፍተኛ ክፍተት ነበር::ያንን በማሻሻል በ24 ሰዓት ውስጥ እየተተገበረ ይገኛል::››

እንችላለን::አቅማችን እና ልንሰራ የሚገባን ነገር እንደሚራራቅ ግልፅ ነው::ስለዚህ ከአሁኑ ከአቅማችን በላይ መስራት መጀመር አለብን:: ሕብረተሰቡም የወረርሽኙን አሳሳቢነት በቅጡ በመረዳት በቂ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ሊገነዘብ ይገባል::

**የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ወረርሽኙን ለመቆጣጠር እስካሁን ሲያደርገው የነበረውን ጥረት እንዴት ይመለከቱታል? ሚኒስትር መ/ቤቱ ላይ ምን ክፍተትስ ታዘቡ?**

በእርግጥ ሚኒስተር መስሪያ ቤቱ ለመስራት እየሞከረ ያለው ነገር የሚያስመሰግነው ነው::እንደ ፓርቲ ከሁሉም በፊት መግለጫ በማውጣት የተለያዩ ምክረ ሃሳቦችን አቅርበን እንደነበር ይታወሳል::ያነሳናቸው ምክረ ሃሳቦች ተግባራዊ ተደርገዋል ብለን እናምናለን::እንደምሳሌ በተደጋጋሚ ስንል የነበረው በቋሚነት ለማኅበረሰቡ መረጃማ ድረስ ላይ ከፍተኛ ክፍተት ነበር::ያንን በማሻሻል በ24 ሰዓት ውስጥ እየተተገበረ ይገኛል::እርግጥ አሁንም ዝርዝር መረጃዎቹን ማኅበረሰቡ በሚረዳው መልኩ ማቅረብ ላይ ክፍተቶች አሉ::አሁን ደግሞ የምናቀርበው ምክረ ሃሳብ የሚሆነው ጥናቶች እንዲሰሩ ነው::በሃገራችን በሽታው በዋነኝነት የቱን የዕድሜ ክልል እያጠቃ ነው? ምን አይነት የማህበረሰብ ክፍል ይበልጥ ተጋላጭ ሆነ?የበሽታው ዓይነትስ ምልክት የማያሳይ?ቀላል?መካከለኛ ወይስ አደገኛ የሚባል ነው?የመሳሰሉ....ጥናቶች ተሰርተው ስርጭቱን ከመቆጣጠር አንጻር የሚረዱ ድምዳሜዎችን ወደ ተግባር ማምጣት ዋነኛ ስራ መሆን ይኖርበታል:: እነዚህ መረጃዎች ላይ መስራት በተለየ መልኩ የማኅበረሰቡን ግንዛቤ ከፍ በማድረግ ልዩ ጥንቃቄ እንዲደረግ ትልቅ ሚና ይኖረዋል::

**የአፍና የአፍንጫ ጭምብል ማድረግ በቫይረሱ የመጠቃት እድላችንን ከመከላከል ወይም ከመቀነፅ አንፃር ፋይዳው ምን ያሕል ነው? የመንግሥት የፀጥታ ሀይሎች የአፍና የአፍንጫ ጭምብል ያላደረጉ ዜጎችን በማሰር ላይ ይገኛሉ:: ከእስር እርምጃ በተጨማሪ በየመንገዱ እያስቆሙም ድብደባ ያካሄዳሉ:: ይህን መሰል የጉልበት እርምጃ እንዴት ይመለከቱታል?**



ይህን ወረርሽኝ እንደ ፖለቲካ መሳሪያ መጠቀም በማኅበረሰቡ ዘንድ ትዝብት ውስጥ የሚጥል ያነሰ ተግባር ነው::

የአፍና የአፍንጫ ጭምብል መጠቀም መልካም ነው ፋይዳውም በቀላሉ የሚታይ አይደለም::ቢያንስ በማስነጠስ ሰዓት የሚወጡትን እርጥበታማ ፈሳሾች ይከላከላል::ነገር ግን መረሳት የሌለበት ጉዳይ እንዴት እና ምን አይነት ጭምብል እንጠቀም?የሚል ነው:: ጭምብል አጠቃቀም ላይ በቂ የሚባል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ አልተሰራም::ከሁሉም በላይ ግን ሊኖረን የሚችለው የአቅርቦት ጉዳይ ታሳቢ መሆን አለበት::ይህም ማለት አቅርቦት ላይ በሚገባ መስራት አለበት ማለት ነው:: እስካሁን ባለው መረጃ አስተማማኙ መከላከያ መንገድ እራስን ከግንኙነት ማቀብ ነው፤ከቤት አለመውጣት ማለት ነው:: የጭንብሎቹ የመከላከል መጠን የሰማይና የምድር ያህል የሚራራቅ ነው:: ጭምብሉን ማድረግና ማውለቅ ብሎም አወጋገዱ ላይ ምንም ሲባል አይሰማም::የምንጠቀመው ጭምብል ርቀትን ከመጠበቅ አንጻር ያለው አገልግሎት ሊታሰብበበት ይገባል:: ጭምብል ስላደረክ ብቻ ደህንነትህ ይጠበቃል ማለት አይደለም:: አካላዊ ርቀትን መጠበቅ መሰረታዊ ጉዳይ ነው:: ስለዚህም በዋነኝነት ከቤት አለመውጣት፤ከወጣን ርቀታችንን በሚገባ መጠበቅ እና ተገቢ የሆነ ጭምብል መጠቀም ትክክለኛው የመከላከያ መንገዱ ነው::ከዚያ በተረፈ ግን ግማሽ መጠንቀቅ የሚባል ሳይንስ የለም::

በጸጥታ ሃይሎች እየተደረገ ያለው ድርጊት ግን ዓላማ የለሽ ሕዝብ ማሸበር ነው፣ ሊወገዝ ይገባዋል!በመሰረታዊነቱም ሰብዓዊ መብትን መጣስ ነው::ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ካለን አቅም በላይ ማሰብም መስራትም ያለብን ለእንደዚህ አይነት በአመለካከት ላይ ለምናመጣው ለውጥ ነው:: ይህን ማሳካት ዋነኛው ግብ አድርገን እያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ ማድረግ ነው::ይህ ደግሞ የሚሳካው በግዳጅና በእስር ሳይሆን በበቂ እውቀትና ግንዛቤ ነው፤እገዛውም ግድ ነው::

**አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች የኮሮና ወረርሽኝ በአጭር ጊዜ ሊገታ የሚችል ስላልሆነ ማኅበረሰቡ አስፈላጊ ጥንቃቄ እያደረገ እንቅስቃሴውን መቀጠል አለበት እንጂ እንቅስቃሴውን ገቶ እንዲቀመጥ ማድረግ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ብሎም የፖለቲካ ቀውስ ሊያመጣ ስለሚችል የተገቱ እንቅስቃሴዎች መቀጠል አለባቸው ይላሉ:: እርስዎ የእነዚህን አስተያየት ሰጪዎች አስተያየት እንዴት ይመለከቱታል?**

በዚህ ረገድ እንኳን መንግስት እየወሰደ ያለው እርምጃ መልካም የሚባል ነው፤ ሁሉንም መዝጋት ወይም ሁሉንም መክፈት አንችልም::አሁን እየተወሰደ ያለው እርምጃ መቀጠል ነው ያለበት::እስካሁን ያለው ስርጭት ላይ በቂ ጥናት ካደረግን በኃላ ነው ቀጣይ እርምጃዎችን መወሰን ያለብን::በኢኮኖሚው ዘንድ ለሚያጋጥመን ችግር ድጋፎችን አጠናክሮ መቀጠል እስካሁን የተሰበሰበው ሃብት በምን መልኩ እየተሰተናገደ መሆኑን ለማኅበረሰቡ በየጊዜው እያሳወቁ ትብብር እና መደጋገፉ እንዲቀጥል ማድረግ ነው::

**የኮሮና ወረርሽኝ በሀገራችን ላይ የሚፈጥረውን የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ ቀውስ እንዴት መወጣት ይቻላል ብለው ያምናሉ?**

ይህ ሃሳብ ሰፋ ያለ እይታ ይፈልጋል::አሁን ላይ ድምዳሜ መስጠትም ያስቸግራል ብዬ አምናለሁ::ካለሁ ሁኔታ ተነስተን ማለት የምንችለው አንድ ነገር ቢኖር ግንእኛ ብቻ አይደለንም ሁሉም ዓለም ቁጭ ብሎ እንዲያስብና አስተምህሮቶች ላይ በቂ ጥናት ሊያደረግ እንደሚገባ ነው::በዚህ መልኩ ግን መቀጠል እንደማንችል መገመት ከባድ አይደለም::ዓለም በትብብር እና መደጋገፍ ብሎም አብሮ ስለማደግ እንዲያስብ ይገደዳል ብዬ አስባለሁ::ቆንጆ አፍሪካዊ አባባል አለ::‹‹ሩቅ ለመሄድ አብረህ ተጓዝ››የሚባል እናም የሰው ልጆች አብረን ከመጓዝ ውጪ የተሻለ አማራጭ እንደሌለን የሚያሳይ ክስተት ነው::በአጭሩ አዲስ መንገድ እና አስተሳሰብ አምጥተን ነው ቀውሱን መወጣት የምንችለው ብዬ ነው የማምነው::እንደኛ ላለ ሀገር ከፖለቲካው አንጻር ቅጥ ያጣ ክፍፍላችንን ለመቀነስና በጋራ መስራት ለመጀመር ምክንያት ሆኖ እንዲያገለግል ምኞት አለኝ::

**ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መንግሥትን ከመተቸት በዘለለ ወረርሽኙን ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት ምን አይነት ሚና መጫወት አለባቸው ይላሉ?**

በዚህ ወቅት ተቃዋሚ ወይም ተፎካካሪ የሚባል አስተሳሰብ ሊኖር አይገባም::ወረርሽኙ እንደምታውቀው ብሄር አይመርጥም::ይሄ የኔ ክልል ነው፤እዚህ አትምጣ እዚያ አትሂድ የምትለው አይደለም::በተለይ ስርዓት ያለው መዋቅር ያላቸው ፓርቲዎች መዋቅራቸውን ተጠቅመው ማኅበረሰቡን ግንዛቤ ማስጨበጥ ላይ ከፊት መሰለፍ አለባቸው ብዬ አምናለሁ::ኢዜማ ይህን ነው እየሰራ ያለው::እንደ ዜጋ አባሎቻችን ለራሳቸው መጠንቀቅ አለባቸው፤እንደ ፖለቲካ ፓርቲ አባልነታቸው ደግሞ ከፍ ያለ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል::በተለይ ለኢዜማ አባሎች ማለት የምፈልገው ደም የመለገስ ዘመቻው ላይ እንዳደረግነው ርብርብ ሁሉ ማኅበረሰቡን ግንዛቤ ለማስጨበጥ መትጋት እንዳለብን ነው:: ሌሎች ፓርቲዎችም ቢሆኑ ያላቸው አደረጃጀት ያን ያህል ሰፊ ባይሆንም ባላቸው አቅም መስራት እንዳለባቸው አስባለሁ::

**በእርስዎ በኩል እንደ መደ ምደሚያ የሚያነሱት ሀሳብ ካለ?**

ይህን ወረርሽኝ እንደ ፖለቲካ መሳሪያ መጠቀም በማኅበረሰቡ ዘንድ ትዝብት ውስጥ የሚጥል ያነሰ ተግባር ነው:: ይህን የዘቀጠ ድርጊት እያደረጉ ያሉ የመንግሥት አካላት ከዚህድርጊታቸው ሊታረሙ ይገባል::መጪው ጊዜ እንኳን እርስ በእርስ ተገፋፍተን ቀርቶ እንደ ሕዝብ አብረን ቆመንም እንዳይጥለን ያስፈራል:: ያለን የተሻለው አማራጭ ተደጋግፈን ማኅበረሰባችንን ከመጣው ወረርሽኝ እራሱን እንዲጠብቅ ማድረግ ነው::ፓርቲ ወይም ድርጅት ግብ አይደለም፤ወደ ግባችን የምንደርስብት መንገድ እንጂ::እናም ሀገራችንን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማሸጋገርም ሆነ ስልጣን ለመያዝ የሕዝብ መኖር ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ሊሆን ይገባል::ይህን ከልቡ አምኖ ነው ኢዜማ እየሰራ ያለው::ይህን እውነታ ዘንግተው ርካሽ መንገድ ላይ ላሉ አካላት አካሄዳቸውን ቆም ብለው እንዲገመግሙ ለማሳሰብ እወዳለሁ:: የትም በማያደርሰን መንገድ ላይ ባንሸቀዳደም ይሻላል::ማናችንንም አሸናፊ አያደርግም::ይበልጥ እንደ ሀገር አቅማችንን በታትኖ ውጤት እንዳይኖርን ያደርገናል እንጂ::በዚህ ወቅት ዋናው ነገር ጤና ነው::ሁላችንም በጥንቃቄ እና በማስተዋል ይህን ጊዜ ለማለፍ በአትኩሮትና በጥንቃቄ እንንቀሳቀስ ለማለት እወዳለሁ፤አመሰግናለሁ::

# ቅኝት

በዛሬው የቅኝት አምዳችን በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)ወረዳ 12/13 ላይ እንቃኛለን፡፡ ወረዳ 12/13 ቢሮውን መሀል አራት ኪሎ ግንፍሌ አካባቢ ባለው አፍቅሬ ህንፃ 3ኛ ፎቅ ላይ ከፍቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ምርጫ ወረዳው በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ አይረሴ ታሪክ ሰርተው ያለፉ አሁንም ከፊታቸው ባለው የኢትዮጵያ ፖለቲካ አያሌ ታሪክ ሰርተው ለማለፍ የተዘጋጁ ወጣቶች ያሉበት ወረዳ ነው፡፡እኛም በዛሬው የቅኝት አምዳችን በዚህ ወረዳ ላይ ትኩረት አድርገናል፡፡ ከዚህ በታች የሰፈረውን መረጃ የሰጡን የኢዜማ ምርጫ ወረዳ 12/13 ሊቀመንበር የሆኑትን አቶ ያሬድ ዓለማየሁን እናመሰግናለን፡፡




**የምርጫ ወረዳው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የተዋቀሩበት መንገድና በምርጫ ወረዳችሁ ውስጥ ያሉ አባላት ብዛት**

የምርጫ ወረዳው የሥራ አስፈፃሚ አባላት መረጣ የተካሄደው የፓርቲው ደንብ በሚፈቅደው መሠረት የተከናወነ መሆኑንና በወረዳው ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ እንደሆነ ሊቀ መንበሩ ይናገራሉ፡፡ አጠቃላይ የወረዳው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት 16 ሲሆኑ፤ይህ የሥራ አስፈጻሚ ከኢዜማ ምስረታ ሁለት ሳምንት ቀደም ብሎ የተዋቀረ ነው፡፡አሁን ላይ በምርጫ ወረዳው በሙሉ አቅማቸው የሚሰሩ ከ150 በላይ አባላት እንደሚገኙ ሊቀመንበሩ ጠቁመዋል፡፡

**በምርጫ ወረዳው ያለው የሴቶች ተሳትፎ ምን ይመስላል**

በምርጫ ወረዳው ያለው የሴቶች ተሳትፎ የሚጠበቀውን ያህል ባይሆንም፣ፖለቲካ ውስጥ ደፍሮ የመግባት ችግር እንደብዙዎቹ የኢትዮጵያ ሴቶች ሁሉ በዚህም ወረዳ ላይ ተስተውሏል፡፡ በተለይም የምርጫ ተወዳዳሪዎችን ማግኘት እጅግ ፈታኝ የነበረ ቢሆንም ከሴቶች ጉዳይ ኃላፊዋ ጋር በመሆን በተሠራው ሥራ እስከ አሁን ወደ 30 የሚጠጉ ሴቶችን በአባልነት ለማቀፍ እንደተቻለ ሊቀመንበሩ ያስረዳሉ፡፡ በምርጫ ወረዳው አባል የሆኑ ሴቶች ለፖለቲካው የዳር ተመልካች እንዳይሆኑና እንዳይርቁ በቂ ክትትል እና ሥልጠና ለመስጠት መሞከሩን የምርጫ ወረዳው ሰብሳቢ ይናገራሉ፡፡

**.የምርጫ ወረዳው ጠንካራ ጎን የሚባለውና የሠራው ተጠቃሽ ሥራ**

የምርጫ ወረዳው ብዙ አንጋፋና ወጣት ፖለቲከኞች የሚገኙበት አካባቢ መሆኑ አንዱ ጠንካራ ጎኑ ሲሆን ሌላው ደግሞ የፓርቲው ግርማ ሞገስና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የራሳቸውን አሻራ ያሳረፉ እንደ አንዱዓለም አራጌ ያሉ ፖለቲከኞች በወረዳው መገኘታቸውም የወረዳው ትልቁ ጥንካሬ መሆኑን ሊቀመንበሩ ይገልፃሉ፡፡ ከአባላት ጋር የተደረጉ ውይይቶች፣ከወረዳው ነዋሪዎች ጋር የተደረጉ ሕዝባዊ ስብሰባዎች፣ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ለአባላት ተከታታይ ሥልጠናዎችን መስጠት መቻሉ በምርጫ ወረዳው ከተከናወኑ ሥራዎች መካከል ተጠቃሽ ሥራዎች ናቸው፡፡ ከሁሉም ጎልቶ የሚወጣው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ቁርጠኛ መሆን የወረዳው ትልቁ ጥንካሬት ደርጎ መወሰድ እንዳለበት ሰብሳቢው አስረድተዋል፡፡ አመራሮቹ ለቢሮ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ከኪሳቸው ገንዘብ አውጥቶ ከማሟላት ጀምሮ እንደ አስፈላጊነቱ በየሳምንቱ እየተገናኙ የተለያዩ ስራዎችን ለመከወን እየጣሩ ይገኛሉ፡፡

**የምርጫ ወረዳው ጥናትና ምርምር ኮሚቴ የአካባቢውን ነዋሪ ችግር አጥንቶ በመለየት ደረጃስ የሠራው ሥራ ሲገመገም**

የወረዳው የጥናትና ምርምር ክፍል«ወደኅብረተሰቡ ወርዶ ሥራ ሠርቷል!»ለማለት እንኳን አያስደፍርም። የወረዳው ትልቁ ድክመት ይህ ነው፡፡ መጠይቆች ተዘጋጅተው ካለቁ ከኋላ ወደ ትግበራ ለመግባት አለመቻሉ እንደ ትልቅ ክፍተት ታይቶ በሥራ አስፈጻሚ ደረጃ ውይይት ተካሄዶበት ግምገማ መካሄዱን ሰብሳቢው ጠቁመዋል፡፡ በቅርቡም ከሌሎች ወረዳዎች ተሞክሮ በመውሰድ ወደ ተግባር ለመግባት ዝግጅት እየተደረገ የነበረ ቢሆንም በተከሰተው የኮሮና ወረርሽኝ የተነሳ የወረዳው ዕቅድ ዳር ሳይደርስ ሊቋረጥ ችሏል ፡፡

**. በምርጫ ወረዳው ውስጥ ያሉ ቀበሌዎች እና ያሉ የምርጫ ጣቢያዎች ብዛት**

በምርጫ ወረዳው 21 የሚሆኑ ቀበሌዎች እና 6 ያህል የአስተዳደር ወረዳዎች ሲገኙ በድሮው 88 የምርጫ ጣቢያዎች ይገኛሉ፡፡

**.በምርጫ ወረዳው ያለው አደረጃጀት፣በአደረጃጀት ጊዜ ያጋጠሙ ፈተናዎችና መልካም ነገሮች**

የወረዳው አደረጃጀት ወደ ታች ወደ ኅብረተሰቡ በተለይም በቀበሌ ደረጃ ያሉ ሴሎችን ለማዋቀር ሙከራ ተደርጓል፡፡ በየቀበሌው ተጠሪዎች እንዲኖሩ ለማድረግ እና ከወረዳው ጋር በቅርብ የሚሠራ ኮሚቴ እስከ ማዋቀር የተደረሰበት ሂደት ተፈጥሯል፡፡ በማደራጀት ሂደት ውስጥ የነበሩ ዋና ፈተና ተብሎ የሚነሳው ዋና ነገር በተለያየ ጊዜ ሊደረጉ በሚታሰቡ ስብሰባዎች ላይ አባላቱ ተሟልቶ አለመገኘት ዋነኛው ሆኖ ይገኛል ይላሉ ሊቀመንበሩ፡፡ መልካም ጎኑ ደግሞ ለማደራጀት ደከመኝን የማያውቁ አባላት ሁሌም ከአመራሮቹ ጎን መሆናቸው እንደሆነ በጉልህ ይጠቀሳል ባይ ናቸው ሊቀመንበሩ፡፡

7.የኢዜማን ራዕይ፣ ተልዕኮና ግብ ለወረዳው ነዋሪዎችና አባላት ማስተዋወቅ ላይ የተሰራው ሥራ

አባላቱን በተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ በማቀፍ ሥልጠናዎች እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይቶችን ለማድረግ ሙከራ አድርገናል የሚሉት ሰብሳቢው በተጨማሪም በሶፍት ኮፒ እና በሀርድ ኮፒም አንዳንድ ሰነዶችን ለእያንዳንዱ አባል በእጅ እንዲደርስ መደረጉን ያስረዳሉ፡፡ ቢሮው በተቻለ መጠን ክፍት እንዲሆን በማድረግም የአባላት ጥያቄን ለማስተናገድ መሞከሩን ሊቀመንበሩ ጠቁመዋል፡፡

**የምርጫ ወረዳው በራሱ ያዘጋጀው ዓመታዊ እቅድ አለው**

ሁሉም በተለይ ደግሞ የሴቶች፣ የወጣቶች፣የሙያ ማኅበራት፣ የሕዝብ ግንኙነት፣እንዲሁም የድርጅት ጉዳይና የጥናትና ምርምር ተጠሪዎች ዓመታዊ እቅድ እንዲያዘጋጁ በማድረግ የተሠራ ቢሆንም እቅዱ የ2012 ዓ.ም ምርጫ ይካሄዳል ከሚል ግምት አንጻር ቢታቀዱም በኮሮና ምክንያት እንደ እቅዱ መጓዝ አለመቻሉን ሊቀመንበሩ ይገልፃሉ፡፡

**አዳዲስ አባላትን ለማምጣትና ለመመልመል የተደረገው እንቅስቃሴ**

አዳዲስ አባላትን ለመመልመል ሁነኛው የወረዳው እቅድ የቀበሌ አደረጃጀትን በሚገባ መጠቀም ላይ ያተኮረ ሲሆን ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ማዘጋጀትና የወረዳውን ማኅበራዊ ሚዲያንም ተጠቅሞ ፓርቲውን በማስተዋወቅ አዳዲስ አባላትን የመመልመል ሥራ መሠራቱን ሊቀመንበሩ ይናገራሉ፡፡

**ነኢዜማን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ሆነ በአዲስ አበባ ምክር ቤት በተሻለ ሊወክሉ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ለማሳተፍ የተደረገውጥረት**

ለምርጫ ጠንካራ ተወዳዳሪዎችን ወደፊት ለማምጣት የተሠሩት ሥራዎች ያልተጠናቀቁ ቢሆኑም በተቻለ መጠን ግን ሰዎችን በማናገርና በማሳመን ወደ ውድድር መድረኩ እንዲመጡ መደረጉንና ቀጣይ ሥራዎች እንደሚቀጥሉ በተለይ ሴት ተወዳዳሪዎችን በብዛትና በጥራት ወደ ፊት ለማምጣት እንደሚሠራ ሊቀመንበሩ ገልጸዋል ፡፡

**ከኮሮና ቫይረስ ጋር ተያይዞ ወረዳው ምን እየሰራ ያለው ሥራ**

ከኮሮና ጋር በተያያዘ ብዙ የግንዛቤ ማስጨበጫ መልዕክቶችን በቴሌግራም ቻናል እንዲሁም በፌስቡክ ገጽ ለአባላትና ለነዋሪው ኅብረተሰብ መልዕክትና መረጃ በማስተላለፍ ላይ እንደሚገኙ ሊቀመንበሩ ጠቁመዋል፡፡ ለወረዳው ኅብረተሰብ የተደረገው ሌላው ትልቁ የግንዛቤ ማስጨበጫ በበዓለ ፋሲካ ወቅት በመኪና በመዞር ከኮሮና ራሳቸውን እንዲጠብቁ መልዕክቶችን ማስተላለፍ መሆኑን ሊቀመንበሩ አስረድተዋል፡፡

**. ኮሮና ቫይረስ በምርጫ ወረዳው ሥራ ላይ የፈጠረው መስተጓጎል**

በዋነኝነት ወረርሽኙ ያሳደረው ጫና እንደ ልብ ከአባላቶቻችን ጋር አለመገናኘት መሆኑንና በዚህም የተነሳ አብዛኛው አባል ቢሮ እየመጣ ወርኃዊ መዋጮ እየከፈለ አለመሆኑን ሊቀመንበሩ ገልፀዋል፡፡በዚህም የተነሳ ከጊዜ ወደ ጊዜ የወረዳውን የፋይናንስ አቅም ፈተና ላይ መውደቁን ሊቀመንበሩ ተናግረዋል፡፡

**በወረዳው ያሉ ነዋሪዎች ስለ ኢዜማ ያላቸው እሳቤ**

የወረዳው ነዋሪዎች ስለ ኢዜማ ያላቸው አመለካከት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን ለማወቅ መቻሉን ሊቀመንበሩ ይናገራሉ፡፡ አሉባልታዎች ፓርቲውን ብዙ ዋጋ እንዳስከፈሉት ቢታወቅም ኅብረተሰቡ ግን በተቻለው አቅም ስለ ፓርቲው እውነታውን እንዲያውቅ ለማድረግ መጣሩን፣ በተለይ ግን ወጣቱ ላይ ብዙ መሥራት እንደሚያስፈልግ ሊቀመንበሩ ያሬድ አለማየሁ ገልጸዋል፡፡

**ኢዜማ ምርጫውን አሸናፊ ሆኖ ቢወጣ ለአካባቢው ነዋሪም ሆነ ማኅበረሰብ ምርጫ ወረዳ ሊሰራ የተዘጋጀው ስራ**

ወረዳው ልክ እንደሌሎቹ ወረዳዎች ሁሉ ማኅበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጫናዎች ያሉበት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ኢዜማ በሚያምንበት«በማኅበራዊ ፍትህ»የፖለቲካ ፍልስፍና መሠረት የአብዛኛውን ደሃ ማኅበረሰብ ችግር በመቅረፍ ኢዜማ የተሻለ ፓርቲ መሆኑን ለማሳየት እንደሚጥር የወረዳው ሊቀመንበር አቶ ያሬድ ዓለማየሁ ተናግረዋል፡፡



## ምርጫ ወረዳዎች ስለ ኮሮና ወረርሽኝ ሕብረተሰቡን በማንቃትና ግንዛቤ በማስጨበጥ እንዲሳተፉ ጥሪ ቀረበ

የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን ተከትሎ ‹‹አሁንም እጠንቀቅ፤ አንዘናጋ!›› በሚል መሪ ቃል ኅብረተሰቡን የማንቃትና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ከግንቦት 27 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ለመሥራት ዝግጅቶች እየተደረጉ እንደሚገኙ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የጤና ፖሊሲ ቡድን አስተባባሪ እና የኮቪድ 19 ግብረ ኃይል ሰብሳቢ ዶ/ር ሙሉዓለም ተገኘወርቅ ለዜጎች መድረክ ገለፁ ፡፡

የግብረኃይሉ ሰብሳቢ ከዚህ ቀደም ፓርቲያቸው ኢዜማ ወረዳዎችን በማስተባበር በኢትዮጵያ ተከስቶ የነበረውን የደም እጥረት ለመቅረፍ የደም መለገስ መርሃ ግብር በሀገር አቀፍ ደረጃ አዘጋጅቶ እንደ ነበር አስታውሰዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተወሰኑ የምርጫ ወረዳዎች እርዳታ ለሚሹ ወገኖች ድጋፍ አድርገው እንደ ነበር አውስተዋል፡፡ የማኅበረሰቡ የወረርሺኙ ስርጭትን ለመግታት መደረግ ያለበት ዋነኛው ነገር ማኅበረሰቡን ግንዛቤ ማስጨበጥ ላይ ባለመታከት በተለያዩ መንገዶች መሥራት ነው ያሉት ዶ/ር ሙሉዓለም ኅብረተሰቡም የወረርሽኙን አሳሳቢነት በቅጡ በመረዳት በቂ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ሊገነዘብ ይገባል ብለዋል፡፡ኅብረተሰቡ ስለ ወረርሽኙ ያለው ግንዛቤ ሲያድግ አስፈላጊ ጥንቃቄ ማድረጉ እንደማይቀር የሚያስረዱት ዶ/ር ሙሉዓለም፣ ኅብረተሰቡን የማንቃትና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራበት እንደሚገባ በአፅንኦት ተናግረዋል፡ ፡ ኅብረሰቡን ለማንቃትና ግንዛቤውን ለማሳደግም ‹‹አሁንም እንጠንቀቅ፤ አንዘናጋ!›› በሚል መሪ ቃሪ ቃል ፓርቲያቸው ኢዜማ ኅብረተሰቡን የማንቃትና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ መሥራት አስፈላጊ ሆኖ እንዳገኘው ገልፀዋል፡፡

ኅብረተሰቡን የማንቃትና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ለመሥራት ዝግጅቶች ማድረጋቸውን የሚገልፁት የጤና ፖሊሲ ቡድን አስተባባሪው‹‹አሁንም እጠንቀቅ፤ አንዘናጋ!››በሚል መሪ ቃል በሚዘጋጀው የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብር ላይ እያንዳንዱ የምርጫ ወረዳ ኅብረተሰቡን በማንቃትና ግንዛቤ በማስጨበጥ በንቃት እንዲሳተፍ ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡